23. Qajeelino manni wolqa burqisanna ikkadimma lossate ispoortete rosi, qajeelshinna xiinxallote uurrinshuwa uurritanno hayyo malatenni loosoho hossanno gede assitanno.
24. Ispoortete wo’naalshi darguwanna ispoortete bowirshi mereershuwa halashshitanno.
25. La’annonsa bisubba ledo buusamatenni ispoortete xagishshi owaante uurrissanno.
26. Ispoortete garimalu jawaachishshi dhagganna araadote udiinne horoonsi’ra gargarate dandiissanno amuraate diriirsitanno.

የአስተዳደር እና ሌሎች እሴቶች በሀገርና ዓለም አቀፍ ደረጃ በተገቢው እንዲታወቁ ይሰራል፣

20. በክልሉ የተለያዩ የመዝናኛና አማራጭ ሰው ሰራሽ የቱሪዝም ማዕከላትን ይገነባል፣ ያስተዳድራል፣ ያስፋፋል፡፡
21. የባህል፣ ስፖርትና ቱሪዝም መረጃዎችን ያሰባስባል፣ ያጠናቅራል፣ ያሰራጫል፡፡
22. ህዝቡን በስፖርት ለሁሉምና ባህላዊ ስፖርት ተሳታፊና ተጠቃሚ ያደርጋል፡፡
23. የሰለጠነ የሰው ሃይል ማፍራትና ብቃትን ለማሳደግ የስፖርት ትምህርት፣ ሥልጠናና ምርምር ተቋሞች የሚቋቋሙበትን ሥልት በመቀየስ ተግባራዊ እንዲሆን ያደርጋል፡፡
24. የስፖርት ማዘውተሪያ ሥፍራዎችንና የስፖርት ማበልጸጊያ ማዕከላትን ያስፋፋል፡፡
25. ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር የስፖርት ህክምና አገልግሎት ያደራጃል፡፡
26. በስፖርት አበረታች መድሃኒቶችና ዕፆች መጠቀምን ለመላከል የሚያስችል ሥርዓት ይዘረጋል፡፡

27. Heewonna feestivaale qixxeessatenni ispoortete handaarita eote safo halashshitanno; dagoomu beeqqonna horaameessimma lossitanno.
28. Qoqqowoho uuritanno ispoortete mamarrara fajoote uytanno; qorqortanno; irkissanno; buusansiissanno; investerootu ispoortete handaara e’e beeqqo assitanno gara injeessitanno; federaalete deerrinni uurritino ispoortete maamarra borreekkitanno; hasiissanno irko assitanno.
29. Hexxo jeefa gansiisate kaa’liatannota wole assootubba assitanno.

**N) Loosu Kaayyo Kalaqate, Industiretenna Interprayizete Biiro**

1. Qoqqowu giddo looso hasidhanno addinnii wedellunna meyati looso kalaqate hala’ladunni bobbakkanno gede huwanyo kalaqate, qajeelishunni irkisate, loosu base injeesate, liqoote, dikkote xaadooshshi amaalenna woloota kaa’lo afidhanno gede assitanno; injo kalaqqanno.

2. Industirete qachubba, sheedubba, paarkubbanna kilaasterubba halashshitanno, gatamartanno,

27. ውድድሮችንና ፌስቲቫሎችን በማዘጋጀት የስፖርቱ ዘርፍ የገቢ መሠረቶችን ያሰፋል፣ የህብረተሰቡን ተሳትፎና ተጠቃሚነት ያሳድጋል፡፡
28. በክልሉ ለሚቋቋሙት የስፖርት ማህበራት ፍቃድ ይሰጣል፣ ይቆጣጠራል፣ ይደግፋል፣ ያስተባብራል፣ ኢንቨስተሮች በስፖርት ዘርፍ ገብተው ኢንቨስት እንዲያደርጉ ሁኔታውን ያመቻቻል፣ በፌደራል ደረጃ የሚቋቋሙ የስፖርት ማህበራትን ይመዘግባል፣ አስፈላጊውን ድጋፍ ይሰጣል፡፡
29. ዓላማውን ለማስፈጸም የሚረዱ ሌሎች ተግባራትን ያከናውናል፡፡

**ኀ)የሥራ ዕድል ፈጠራ፣ ኢንዱስትሪና ኢንተርፕራይዞች ቢሮ**

1. የክልሉ ሥራ ፈላጊዎች በተለይም ለወጣቶች እና ለሴቶች በስራ ፈጠራ ላይ በስፋት እንዲሰማሩ ግንዛቤ ይፈጥራል፣ የስልጠና ድጋፍ፣ የመስሪያ ቦታ፣ ብድር፣ ገበያ ትስስር ምክር እና ሌሎች ድጋፎች እንዲያገኙ ያደርጋል፣ ያመቻቻል፡፡

2. ኢንዱስትሪ መንደሮች፣ ሼዶች፣ ፓርኮች እና ክላስተሮች እንዲስፋፉ፣

hasiisanno qorqorshsha assitanno.

3. Industiretenna ogimmate lifinxe keenate seera loosu aana hosiissanno, silaanchimanna udiinnichu deera hajo la'anonsa bisubba ledo halamatenni tajete woraqatinni buuxissanno.
4. Interpirayzetenna Industirete irko paakeeje qixxeessitanno, qineessitanno, jeefisiissanno, loosu aana hosaseno ha'runsitanno.
5. Manufakcherete laalcho baara widira sokkanno faabrikubbanna Interpirayzoota hajo la'annonsa bisubba ledo halamatenni laalchonsa baara widira sokkanno gede irkissanno.
6. Loosu kaayyo kalaqate amaale mini baalante tantanora uurranno gede assitanno, amaalete minira looso qineesitanno, hasiissanno irko uyitnno.
7. Looso kalaqatenna loosu kaayyo aana xiinxallo assitanno, hajo la'annonsa bisubba shiqishatenni kaajjishiishidhanno, gumulo loosu aana hosase ha'runsitanno.
8. Quchumu sagalete waastinni pirogiraame annimmatenni

እንዲጠናከሩ ያደርጋል፣ አስፈላጊውን ቁጥጥር ያደርጋል፡፡

3. የኢንዱስትሪ የሙያ ብቃት መመዘኛ ህጎችን በስራ ላይ ያውላል፣ የጥራት እና የምርቶች ስታንዳርድ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን በምስክር ወረቀት ያረጋግጣል፣ የምርት ጥራት ደረጃ እንዲያገኙ ይሰራል፡፡
4. የኢንተርኘራይዞች እና ኢንዱስትሪዎች የድጋፍ ፓኬጅ ያዘጋጃል፣ ያቀናጃል፣ ያስፈጽማል፣ በስራ ላይ መዋሉን ይከታተላል፡፡
5. የማኑፋክቸሪንግ ምርቶችን ወደ ውጭ በመላክ ላይ ለተሰማሩ ፋብሪካዎች እና ኢንተርኘራይዞች ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን ምርታቸውን ለውጭ ሀገር እንዲያቀርቡ ያግዛል፡፡
6. የስራ ዕድል ፈጠራ ምክር ቤት በሁሉም ደረጃ እንዲቋቋም ያደርጋል፣ የምክር ቤቱን ስራ ያደራጃል፣ አስፈላጊውን ድጋፍ ይሰጣል፡፡
7. የስራ ፈጠራ እና የስራ እድል ላይ ጥናት ያደርጋል፣ ለሚመለከተው አካል በማቅረብ ሲጸድቅ ስራ ላይ መዋሉን ይከታተላል፡፡
8. የከተማ ምግብ ዋስትና ፕሮግራምን

massagganno, hajo la’annonsa bisubba ledo halamatenni irkissanno, jeefishsha ha’runsitanno, hegeraanchu latishshi ledo waaxo kalaqqanno.

9. Hojji sektere widoonni kalaqantanno seedanna harancho yanna loosu kaayyo jeefishsha ha’runsitanno, irkissanno.
10. Addi addi mootimmate uurrinshshuwa giddonna mootimmatenni loosantanno addi addi pirojektubba widoonni kalaqantanno loosu kaayyo jeefishsha ha’runsitanno.
11. Hexxose loosu aana hosiisate hasiissanno wole hajubba jeefissanno.

**O)Tekiniketenna Ogimmate Qajeelshinna Sayinsetenna Tekinoloojete Biiro**

1. Qoqqowoho ikkitannota tekiniketenna ogimmate qajeelshi pirogiraamma gobboomu deerransa agadhite ha’ransa buuxxanno.
2. Deerrase agadhitino safoniti boodillaananna mereerima tekiniketenna ogimmate rosi qajeelshi kaarkuleeme qixxaabanno gede assitanno; ha’runsitanno; irkissanno.
3. Qoqqowoho industiretenna

በባለቤትነት ያስተባብራል፣ ከሚመለከታቸውም አካላት ጋር በመቀናጀት ይደግፋል፣ አፈጻጸሙንም ይከታተላል፣ ዘላቂነት ካለው የልማት ተግባር ጋርም ያስተሳስራል፡፡

9. በግሉ ሴክተር አማካይነት ሊፈጠሩ ስለሚገባቸው ዘላቂና ጊዜያዊ የሥራ ዕድሎች አተገባበር ይከታተላል፤ ይደግፋል፡፡
10. በተለያዩ የመንግስት ተቋማት ውስጥ እና በመንግስት በሚሰሩ ልዩ ልዩ ፕሮጀክቶች አማካይነት የሚፈጠሩ የሥራ ዕድሎች አፈጻጸም ይከታተላል፡፡
11. ዓላማውን ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስፈልጉ ሌሎች ተግባራትን ያከናውናል፡፡

**ነ) የቴክኒክና ሙያ ሥልጠና እና ሳይንስና ቴክኖሎጂ ቢሮ**

1. በክልሉ የሚከናወኑ የቴክኒክና ሙያ ሥልጠና ፕሮግራሞች አገር አቀፍ ደረጃቸውን ጠብቀው መካሄዳቸውን ያረጋግጣል፡፡
2. ደረጃውን የጠበቀ መሰረታዊ መለስተኛና መካከለኛ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ሥርዓተ-ትምህርት እንዲዘጋጅ ያደርጋል፣ ይከታተላል፣ ይደግፋል፡፡

investimentete millimmo irkissannota safonita boodillaananna mereerimu deerri tekinikete ogimma qajeelshu uurrinshuwa uurrissanno; halashshitanno; gashshitanno.

4. Tekiniketenna ogimmate rosinna qajeelshi kolleejuwanna hakko handaarira bobbakkannore wole qajeelshu uurrinshuwara balaxi-afamooshshunna afamooshshu fajjoote uytanno; haaroonsitanno; deerru woroonni higge leelturo fajjootensa hooltanno.
5. Rosunna qajeelshunniha ogimmate ikkadimma buuxishshi amuraate qixxeessitanno; jeefishshasi ha’runsitanno; illaallissanno.
6. Konni handaarira hojji dureeyyenna mootimmaweelo uurrinsha beeqqitanno gara injeessitanno; jawaachishshanno; hasiissanno irko assitanno.
7. Qoqqowunnita tekiniketenna ogimmate rosinna qajeelshi istiraateeje qixxeessitanno; fajjiniro jeefissanno; jeefisiissanno.
8. Qoqqqowoho taalchunna farcamaanchu tekiniketenna ogimmate qajeelshi tuqishshi hee’ranno gede assitanno.

3. በክልሉ የኢንዱስትሪና የኢንቨስትመንት እንቅስቃሴውን የሚያግዙ መሰረታዊ መለስተኛና መካከለኛ ደረጃ የቴክኒክና ሙያ ሥልጠና ተቋማትን ያቋቁማል፣ ያስፋፋል፣ ያስተዳድራል፡፡
4. ለቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ኮሌጆችና በዘርፉ ለሚሰማሩ ሌሎች ማሰልጠኛ ተቋማት የቅድመ-ዕውቅናና ዕውቅና ፈቃድ ይሰጣል፣ ያድሳል ከደረጃው በታች ሆነው ሲገኙ ፈቃዳቸውን ይሰርዛል፡፡
5. የትምህርትና ሥልጠና የሙያ ብቃት ማረጋገጫ ሥርዓት ያዘጋጃል፣ ተፈፃሚነቱን ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፡፡
6. በዘርፉ የግል ባለሀብቶችና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች የሚሳተፉበትን ሁኔታ ያመቻቻል፣ ያበረታታል፣ አስፈላጊውን ድጋፍ ይሰጣል፡፡
7. የክልሉን የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ስትራቴጂ ያዘጋጃል ሲፈቀድም ይፈጽማል፣ ያስፈጽማል፡፡
8. በክልሉ ተመጣጣኝ እና ፍትሃዊ የቴክኒክና ሞያ ስልጠና ሽፋን እንዲኖር ያደርጋል፡፡

9. Dikkote hasatto mereersinoha rosaminonna rosaminokki qajeelshi pirogiraame roso qixxeessitanno; loosu aana hossanno gede assitanno; karikuleme qixxaabbanno raga leellishshanno.

10. Tekiniketenna ogimmate qajeelshi mereershuwa albillicho fulonsa uminsanni wonshi'ra dandiissitannota eo lossate raga maltanno.
11. Tekiniketenna ogimmate qajeelshi uurrinshuwa gutoomunni qajeelsha uytanno assooti biddissa fushshitanno; jeefishshaho irkissanno; ha'runsitanno.
12. Qoqqowunnita sayinsetenna tekinoloojete hasatto baddanno, hajo la'annonsa bisubba ledo malamatenni hasatto wonshinanni gara injeessitanno.
13. Hajo la'annonsa bisubba ledo halamatenni qoqqowu giddo tekinoloojete paarke uurritanno gede assitanno.

14. Xiinxallote pirotokoole amanyoote qixxeessatenni loosu kaayyo kalaqannori pirotokooletenni irkisantanno gede assitanno, akatoommete xe'ne heedhuro hasiissannota seeru qaafo adhitanno.

9. የገበያ ፍላጎት መሰረት ያደረገ መደበኛ እና መደበኛ ያልሆነ ስልጠና መርሃ-ግብር ትምህርት ያዘጋጃል፣ በስራ ላይ እንዲውል ያደርጋል፣ ስርዓተ ትምህርት የሚዘጋጅበት አቅጣጫ ይነድፋል፡፡
10. የቴክኒክና ሙያ ማሰልጠኛ ማዕከላት ወደፊት ወጪያቸውን በራሳቸው መሸፈን የሚያስችል የገቢ ማሳደግያ የአፈፃፀም አቅጣጫ ይነድፋል፡፡
11. የቴክኒክና ሙያ ማሰልጠኛ ማዕከላት በሽርክና ስልጠና የሚሰጡበትን የአሰራር መመሪያ ያወጣል፣ ለአፈፃፀሙ ይደግፋል፣ ይከታተላል፡፡
12. የክልሉን የሳይንስና የቴክኖሎጂ ፍላጎት ይለያል፣ ከሚመለከታቸዉ አካላት ጋር በመመካከር ፍላጎቱ የሚሟላበትን ሁኔታ ያመቻቻል፡፡
13. ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር በክልሉ የቴክኖሎጂ ፓርኮች እንዲቋቋሙ ያደርጋል፡፡
14. የምርምር ፕሮቶኮሎች ሥነ-ምግባር በማዘጋጀት ሥራ ፈጠራዎቹ በፕሮቶኮል እንዲደገፉ ያደርጋል፣ የሥነ-ምግባር ጉድለት ሲያጋጥም አስፈላጊ የሆነ ህጋዊ እርምጃ ይወስዳል፡፡

15. Qoqqowu giddo heedhannoti sayinsete, tekinoloojetenna kalaqate loossa womaashshunni, udiinichunna tekinikete kaa'lo afidhanno gara injeessitanno, handaara kaajjishate roore dilaala fultino bisubbanna hojji mannoota jawaachishshanno.
16. Qoqqowu giddo heedhanno silaanchimma buuxate xintu latishshanna carare gargarate looso massagganno, jeefisiissanno.
17. Xiinxallotenni anfanni woy kalanqanni sayinsetenna tekinoloojete gumma buqqeete jajji qoosso afidhanno gede irko assitanno.
18. Xaadooshshunna mashalaqqete tekinolooje owaante silaanchimma, keeraanchimmanna ikkadimmansa agarantinota ikkitanno gede assate deerra murtanno, loosu aana hosansano buuxxanno.
19. Mootimmate uurrinshuwa tajete amanyoote xintatenninna waaxatenni mootimmate doomeenete su'ma beekkanno, teesso borressitanno, qorqortanno.

15. በክልሉ የሚካሄዱ የሳይንስ፣ ቴክኖሎጂና ፈጠራ ስራዎች እንቅስቃሴዎች የገንዘብ፣ የማቴሪያልና የቴክኒክ ድጋፎች የሚያገኙበትን ሁኔታ ያመቻቻል፣ ዘርፎችን ለማዳበር የበለጠ አስተዋጽኦ ያደረጉ አካላትንና ግለሰቦችን ያበረታታል፡፡
16. በክልሉ የሚካሄዱ የጥራት መሰረተ ልማትና የጨረራ መከላከያ እንቅስቃሴዎችን ያስተባብራል፣ ተግባራዊም ያደርጋል፡፡
17. በምርምር የሚገኙ ወይም የሚፈጠሩ የሳይንስና ቴክኖሎጂ ውጤቶች የአእምሯዊ ንብረት መብት እንዲያገኙ ድጋፍ ያደርጋል፡፡
18. የመገናኛና የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ አገልግሎቶች ጥራታቸው፣ ደህንነታቸውና አስተማማኝነታቸው የተጠበቀ እንዲሆን የሚያስችሉ ደረጃዎችን ይወስናል፣ ተግባራዊ መደረጋቸውን ያረጋግጣል፡፡
19. የመንግስት ተቋማት የመረጃ ስርዓትን ከመገንባትና ከማቀናጀት አንፃር የመንግስት የዶሜይን ስም ይደለድላል፣ አደራሻ ይመዘግባል፣ ይቆጣጠራል፡፡

20. Qoqqowu Mootimmate uurrinshuwa mereero yannillichu mashalaqqetenna xaadooshshu gishshi xintamasi ha’runsitanno, softiweeretenna sistemete latishshi looso loossanno loosiissanno, hasiissanno irko uytanno, jeefishsha qorqortanno.

21. Mootimmate uurrinshuwa mereero qinaawinonna keeraanchimmasi agarantino mashalaqqete tuqishshi heerranno gede irko assitanno, garunni horote aana hosasi ha’runsitanno.

22. Deerru deerrunkunni heedhanno mootimmate uurrinshuwanna dagoomu bisubba mashalaqqetenna tekinoloojete xiinxallo diizayine qixxeessitanno, yaanillicho mashalaqqete tuqishshi hasatto woy foonqe badate looso loossanno, qarra tirate hedo shiqishshanno, fajjiniro loosu aana hosiissanno.

23. Qoqqowu giddo deerru deerrunkunni heedhanno sektere loosu minna xurqunna mereerima mashalaqqetenna xaadooshshu tekinolooje xintu latishsha loosanno.

24. Qoqqowunniti gashshootu taqqa viidiyote konforaanse, dagoomu mashalaqqete mereerishubba, bilbilu

20. በክልል መንግስት ተቋማት መካከል ዘመናዊ የኢንፎርሜሽን ኮሙኒኬሽን መረብ መዘርጋቱን ይከታተላል፣ የሶፍትዌርና የሲስተም ልማት ሥራን ያከናውናል፣ እንዲከናወን ያደርጋል፣ ተገቢውን ድጋፍም ይሰጣል፣ ተግባራዊነቱን ይቆጣጠራል፡፡

21. በመንግስት ተቋማት መካከል የተቀናጀና ደህንነቱ የተጠበቀ የመረጃ ፍሰትና ልውውጥ እንዲኖር ድጋፍ ይሰጣል፤ በአግባቡ ጥቅም ላይ መዋሉን ይከታተላል፡፡

22. በየደረጃው ላሉ የመንግስት ተቋማትና የሕብረተሰብ ክፍሎች የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ጥናት ዲዛይን ያዘጋጃል፣ ዘመናዊ የመረጃ ልውውጥ ፍላጎት ወይም ክፍተት የመለየት ስራ ያከናውናል፣ የመፍትሄ ሃሳብ ያቀርባል፣ ሲፈቀድም ተግባራዊ ያደርጋል፡፡

23. በክልሉ በየደረጃው ላሉ ሴክተር መስሪያ ቤቶች ውስብስብና መለስተኛ ኢንፎርሜሽንና ኮሚኒኬሽን ቴክኖሎጂ መሰረተ-ልማት ይዘረጋል፡፡

24. በክልሉ የአስተዳደር እርከኖች የቪዲዮ ኮንፈረንሲንግ፣ የማህበረሰብ የመረጃ ማዕከላትን፣ የጥሪ

mereerishubbanna dagoomu raadoonete xaawa uurrissanno, gashshitanno, qorqortanno.

25. Mashalaqqetenna xaadooshshu tekinolooje hojji loosu kalaqo mereerishuwa uurrissanno.
26. Qoqqowunnita mashalaqqete gishsha xintatenna mashalaqqetenna xaadooshshu tekinolooje xintu latishshi looso ha'runsitanno, irkissanno, qorqortanno, latino softiweerenna apilikeeshinnate deera murtanno.
27. Mashalaqqetenna xaadooshshu tekinolooje aana tekinikete qajeelshanna labbanno irko assitanno, lifinxete buuxooshshi fajjo uytanno, loosu aana hosasi qorqortanno.
28. Qoqqowu mootimma mashalaqqetenna xaadooshshu tekinolooje udiinicho horonsha qorqortanno, gatamarantanno gede assitanno, gatamarantannokkita bainore hunsiissanno.
29. Tekinoloojete latishshira womaashshunninna udiinichunni kaa'lo assitara dandiitanno gobba giddonna baara widi bisubba hasate irkonna

ማዕከልና የማህበረሰብ ሬድዮ ጣቢያዎችን ያቋቁማል፣ ያስተዳድራል፣ ይቆጣጠራል፡፡

25. የኢንፎርሜሽን ኮሚኒኬሽን ቴክኖሎጂ የግል ሥራ ፈጠራ ማእከላትን ያቋቁማል፡፡
26. የክልሉን መረጃ መረብ ዝርጋታ እና ኢንፎርሜሽን ኮሚኒኬሽን ቴክኖሎጂ መሠረተ ልማትሥራን ይከታተላል፣ ይደግፋል፣ ይቆጣጠራል፣ የሚለሙ ሶፍትዌሮችና አፕሊኬሽኖችን ደረጃ ይወስናል፡፡
27. በኢንፎርሜሽን ኮሚኒኬሽን ቴክኖሎጂ ላይ የቴክኒክ የስልጠናና መሰል ድጋፎችን ያደርጋል፣ የብቃት ማረጋገጫና ፈቃድ ይሰጣል፣ ተግባራዊነቱንም ይቆጣጠራል፡፡
28. የክልሉ መንግስት የመገናኛና ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ መሳሪያዎችን አጠቃቀም ይቆጣጠራል፣ እንዲጠገኑ ያደርጋል፣ ብልሽታቸው ከአቅም በላይ የሆኑትን ያሰውግዳል፡፡
29. ለቴክኖሎጂ ልማት በገንዘብና በዓይነት ሊረዱ የሚችሉ የአገር ውስጥና የውጭ አካላትን

kaa’lo gamba assate looso massagganno.

30. Hexxose loosu aana hosiisate hasiissanno wole hajubba jeefisiissanno.

**P) Dagitte Owaantenna Mannu Jiro Latishshi Biiro**

1. Qoqqowu mootimma loosaasine filatenna doorate lifinxe kaima ikkitanno gede assitanno, loosu deerrira hasiisanno roso, qajeelishanna loosu rosicho keenate xaphooma bikkancho qixxeesitanno, loosu aana hosiissanno.
2. Qoqqowu mootimma uurrinshuwa assitanno qixire, deerra lossate, base soorate, gaamate, qajeelshunna disippiliine dagate owaante seeri garinni jeefisamasi qorqortanno, assootu so’ro kalaqanturo taashshate qaafo adhitanno.
3. Qoqqowu mootimma loosaasine loosu guma keenate tittirshu biddissa fushshitanno, loosu aana hosiissanno, jeefisamasino ha’runsitanno.
4. Qoqqowu mootimma dagitte owaante lifinxaabbinotanna gummame ikkase buuxxanno.

የማፈላለግና ድጋፍ የማሰባሰብ ሥራን ያስተባበራል፡፡

30. ዓላማውን ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስፈልጉ ሌሎች ተግባራትን ያከናውናል፡፡

**ኘ) የፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ሀብት ልማት ቢሮ**

1. የክልል መንግስት ሠራተኞች ምልመላና መረጣ በብቃት ላይ የተመሰረተ እንዲሆን ያደርጋል፣ለስራ መደቦች የሚያስፈልጉ የትምህርት፣ የሥልጠናና የስራ ልምድ አጠቃላይ መመዘኛዎችን ያወጣል፣ ስራ ላይ ያውላል፡፡
2. በክልሉ የመንግስት መስሪያ ቤት የሚካሄድ ቅጥር፣ የደረጃ ዕድገት፣ ዝውውር፣ ድልድል፣ ሥልጠናና ዲሲፕሊን በፐብሊክ ሰርቪስ ሕግ መሰረት እየተፈፀሙ መሆናቸውን ይቆጣጠራል፣ የአሰራር ስህተት ከተፈፀመ የእርምት እርምጃ ይወስዳል፡፡
3. የክልሉ የመንግስት ሰራተኞች የስራ ውጤት መመዘኛ ዝርዝር መመሪያ ያወጣል፣ በስራ ላይ ያዉላል፣ ተፈፃሚነቱ ይከታተላል፡፡
4. የክልሉ መንግስት ፐብሊክ ሰርቪስ ብቃት ያለውና ውጤታማ መሆኑን

5. Dagitte owaantera mannu wolqa sufamino garinni latisatenna horo uytanno gede assate hayyo kalaqqanno, loosu aana hosase ha’runsitanno.
6. Dagitte owaante uytanori lifinxensanna loosu gummamimansa kaima assino baatoshshunna jawaachishate assooti loosu aana hosanno gede assitanno, gumaamimmasi keentanno, hasiisiro woyyeessate qaafo adhitanno.
7. Qoqqowu mootimma loosaasine akatoomme ha’runsate assooti loosu aana hosanno gede assitanno, jeefishshasi ha’runsitanno.
8. Qoqqowu mootimma loosaasine gashshootu seerubba garunni loosu aana hosansa ha’runsitanno, buuxxanno.
9. Mootimmate haandaari dhuka kaajjishate looso massagganno, mootimmate handaari owaante sufamino garinni woyyaabbannonna gummaame ikkitanno hayyo kalaqqanno, loosu aana hosase ha’runsitanno, keentanno.
10. Qoqqowu mootimma uurrinshuwa tantano gara ikkase buuxxanno, tantano woyyeessate xiinxallo aana irko

ያረጋግጣል፡፡

5. የፐብሊክ ሰርቪሱ የሰው ኃይል በቀጣይነት በሚለማበት ጥቅም ላይ የሚውልበትን ስልት ይቀይሳል፣ ተግባራዊነቱንም ይከታተላል፡፡
6. ለፐብሊክ ሰርቫንቱ በብቃትና በአፈጻፀም ውጤታማነት ላይ የተመሰረተ የክፍያና የማበረታቻ ሥርዓት እንዲዘረጋ ያደርጋል፣ ውጤታማነቱን ይገመግማል አስፈላጊውን የማሻሻያ እርምጃ ይወስዳል፡፡
7. የክልል መንግስት ሰራተኞች ሥነ-ምግባር መከታተያ ስርዓት እንዲዘረጋ ያደርጋል፣ አፈጻፀሙን ይከታተላል፡፡
8. የክልል መንግስት ሰራተኞች አስተዳደር ሕጎች በትክክል ስራ ላይ መዋላቸውን ይከታተላል፣ ያረጋግጣል፡፡
9. የመንግስት ዘርፍ አቅም ግንባታ ስራዎችን ያስተባብራል፣ የመንግስት ዘርፍ አገልግሎት በቀጣይነት የሚሻሻልበትና ውጤታማ የሚሆንበትን ስልት ይቀይሳል ተግባራዊነቱንም ይከታተላል፣ ይገመግማል፡፡
10. የክልል መንግስት መስሪያ ቤቶችን አደረጃጀት አግባብነትን

assitanno.

11. Qoqqowu mootimma uurrinshuwa mannu wolqa horonsi’nanni gara keentanno, woyyeessate hedo shiqishshanno, fajjiniro loosu aana hosase buuxxanno.
12. Qoqqowu mootimma uurrinshuwa owaante uynanni bikka, koffeenya shiqinshaninna tirranni amanyooti qixxaawasinna loosu aana hosasi buuxxanno.
13. Dagitte owaantera mannu jiro massagonna uurrinshate tajete amadooshshi suwashshonna kaajjado ikke loosamanno gede assitanno, mereerima tajete bue ikkite horo uytanno.
14. Qoqqowu mootimma uurrinshuwa mannu jiro gashshoote aliidimmatenni massagganno, loosu massago biddisuwanna jeefishshu bikkaancho qixxeessitanno, jeefisiissanno.
15. Mootimmate loosaasine damooza, barru hoshshonna addi addi aloowaanse woyyeessate xiinxallo assitanno, fajjiniro loosu aana hossanno gede assitanno.

ይመረምራል፣ በአደረጃጀት ማሻሻያ ጥናቶች ላይ አስፈላጊውን ድጋፍ ይሰጣል፡፡

11. የክልሉ የመንግስት መስሪያ ቤቶችን የሰው ሃይል አጠቃቀም ይገመግማል፣ ማሻሻያ ሃሳቦችን ያቀርባል፣ ሲፈቀድም ሥራ ላይ መዋሉን ያረጋግጣል፡፡
12. በክልል መንግስት መስሪያ ቤቶች የአገልግሎት አሰጣጥ ስታንዳርድ፣ የቅሬታ አቀራረብና አፈታት ሥርዓት መዘርጋቱንና ተግባራዊ መደረጉን ያረጋግጣል፡፡
13. የፐብሊክ ሰርቪሱ የሰው ሃብት አመራርና የተቋማዊ መረጃዎች ሥርዓት በወጥነት እንዲዳብርና እንዲተገበር ያደርጋል፣ ማዕከላዊ የመረጃ ምንጭ ሆኖ ያገለግላል፡፡
14. የክልሉን የመንግስት መስሪያ ቤቶችን የሰው ሀብት አስተዳደር በበላይነት ይመራል፣ የስራ አመራር መመሪያዎችና የአፈፃፀም መስፈርቶችን ያዘጋጃል፣ ያስፈፅማል፡፡
15. የመንግስት ሰራተኞችን የደመወዝ፣ የልዩ ልዩ አበሎችና ጥቅማ ጥቅሞች ማሻሻያ ያጠናል ሲፈቀድም ስራ ላይ እንዲውሉ

16. Seeru garinni qoqqowu mootimma loosaasine xuratu diri gedensanni loosu aana keeshshiishate shiqqanno xa’mora gumulo uytanno.
17. Deerru deerrunkunni kalaqantanno danchu gashshootinna muishshu qarra badate xiinxallo, bandoonni rakko ajishate hayyo qixxeessitanno, rakko tirranni gara ha’runsitanno, irkissanno.
18. Horo bade afate xiinxallo assatenni mootimmate owaante aana dagate kassiimma buuxate looso loossanno.
19. Mootimmate loosaasine gashshooti yoo mine qineessitanno, garu seerinni massagamanno gede assitanno.
20. Hexxose loosu aana hosiisate hasiissanno wole hajubba jeefisiissanno.

**Q) Mootimmate Kominikeeshine Biiro**

1. Qoqqowu mootimmanna pirezidaantichu foonii-xawisaancho ikkite loossanno.

ያደርጋል።

16. በሕግ መሰረት የክልል መንግስት ሰራተኞችን ከጡረታ ዕድሜ ክልል በላይ በአገልግሎት ላይ ስለማቆየት በሚቀርቡ ጥያቄዎች ላይ ውሳኔ ይሰጣል።
17. በየደረጀው የሚታዩ የመልካም አስተዳደርና የኪራይ ሰብሳብነት ችግሮችን በጥናት መለየት፣ ለተለዩ ችግሮች ስልቶች በመንደፍ፣ የአፈታት ሂደት ይከታተላል፤ ይደግፋል።
18. የፋይዳ ጥናት በማድረግ በመንግስት አገልግሎት ላይ የህዝብ እርካታን የማረጋገጥ ሥራን ይሰራል።
19. የመንግስት ሠራተኞችን አስተዳደር ፍርድ ቤት ያደራጃል፣ አግባብ ባለው ሕግ መሠረት እንዲመራ ያደርጋል።
20. ዓላማውን ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስፈልጉ ሌሎች ተግባራትን ያከናውናል።

**ለ) የመንግስት ኮሚዩኒኬሽን ቢሮ**

1. የክልሉን መንግስት እና የርዕሰ መስተዳድሩ ቃል አቀባይ ሆኖ ያገለግላል።

2. Qoqqowu mootimma mashalaqqe mereershunni maareekkitenna qineessite hajo la'annonsa bisubbaranna miidiyaho hasiishshu bikkinni tuqissanno.
3. Qoqqowu mereershi sektere uurrinshuwa kominikeeshinetenna miidiyu xaadooshshi looso massagganno.
4. Qoqqowu mootimma dagate xaadooshshi looso loossanno, konforaanse, hasaawu battalanna ikkitubba qineesitanno.
5. Qoqqowu pirezidaantichinna mootimmate miidiyu xaadooshshi looso loossanno.
6. Gobba giddonna baara widi miidiyi odeessaanora hasiisanno bikkinni yanna yannatenni xawishsha uytanno.
7. Miidiya qorqoratenna tittirshu xawishsha qixxeessatenni mashalaqqe pirezidaantichahonna hasiisanno bikkinni hajo la'annonsa bisubbara sayissanno.
8. Miidiyu ikkito aana xiinxallo assitanno, rippoorte qixxeessatenni pirezidaantichahonna hasiisanno bikkinni hajo la'annonsa bisubbara sayissanno.

2. የክልሉን መንግስት ኢንፎርሜሽን በማእከል አደራጅቶ ለሚመለከታቸው አካላት እና ለሚዲያ እንደአስፈላጊነቱ ያሰራጫል፡፡
3. የክልሉ ማዕከል ሴክተር መስሪያ ቤቶችን የኮሚዩኒኬሽን እና የሚዲያ ግንኙነት ስራ ያስተባብራል፡፡
4. የክልሉን መንግስት የህዝብ ግንኙነት ስራዎች ያከናውናል፤ ኮንፈረንሶች፣ ፓናል ውይይቶችን እና ሁነቶችን ያደራጃል፡፡
5. የክልሉን ርዕሰ መስተዳደር እና መንግስት የሚዲያ ግንኙነት ስራ ያከናውናል፡፡
6. ለአገር ውስጥ እና ለውጭ ሚዲያ ጋዜጠኞች እንደየአስፈላጊነቱ በየወቅቱ መግለጫ ይሰጣል፡፡
7. የሚዲያ ሞኒተሪንግና እና ትንታኔ ስራ እያከናወነ መረጃውን ለርዕሰ መስተዳደሩ እና እንደአስፈላጊነቱ ለሚመለከታቸው አካላት ያስተላልፋል፡፡
8. የሚዲያ አዝማሚያ ጥናት ያከናውናል፤ ሪፖርት አዘጋጅቶ ለርዕሰ መስተዳድሩ እና እንደአስፈላጊነታቸው ለሚመለከታቸው አካላት ያስተላልፋል፡፡

9. Yanna yannatenni daga yaadisanno hajubba aana barrunna lamalate dagate hedo gamba assitanno, pirezidaantichahonna hasiisanno bikkinni hajo la’annonsa bisubbara sayissanno.
10. Jawa dagatenna mootimmate hajubbanna polise aana dagate lao xiinxallo assitanno, hajo la’annonsa bisubbara shiqishshanno.
11. Qoqqowu mootimma mashalaqqenna sokka sufamino garinni tuqissanno.
12. Mootimmate mashalaqqe webisayte fantanno, yanna yannatenni heedhanno mashalaqqe mootimmatenni loosamino loosonna jeefishsha hajo la’annonsa bisubbara iillitanno gede assitanno, ha’runsitanno.
13. Miidiyu bacihimma lopha jawaachishshanno, miidiyu mootimmatenna dagate mereero hee’rannosi loosu xaadooshshe massagganno, dagate xa’mo hajo la’anno mootimmate bisubbanni dawaro afidhanno gede assitanno, qara qara qoqqowunna gobbate deerrinni heedhanno ikkito hasiisanno miidiyu reqecco afidhanno gede injeessitanno.

9. በየወቅቱ ህዝብን በሚያሳስቡ ጉዳዮች ላይ ዕለታዊ እና ሳምንታዊ የህዝብ አስተያየት መረጃዎችን ያሰባስባል፤ ለርዕሰ መስተዳድሩ እና እንደ አስፈለጊነታቸው ለሚመለከታቸው አካላት ያስተላልፋል፡፡
10. በትላልቅ የህዝብ እና መንግስት ጉዳዮች እና ፖሊሲዎች ላይ የህዝብ አመለካከት ጥናት ያከናውናል፤ ለሚመለከታቸው አካላት ያቀርባል፡፡
11. የክልሉን መንግስት መረጃ፤ ኢንፎርሜሽን እና መልዕክት በቋሚነት ያሰራጫል፡፡
12. የመንግስት የመረጃ ድህረ ገጽ ይከፍታል፣ በየጊዜው የሚገኘው መረጃ በመንግስት የተሰራ ስራና አፈፃፀም ወደሚመለከተው እንዲደርስ ያደርጋል፣ ይከታተላል፡፡
13. የሚድያ ቡዙህነት ዕድገት ያበረታታል፣ ሚድያ ከመንግስትና ከህዝብ ጋር የሚኖረው የስራ ግንኙነት ያስተባብራል፣ የህዝብ ጥያቄ አግባብ ባለው የመንግስት አካል ምላሽ እንዲሰጥበት ያደርጋል፣ ዋና ዋና ክልላዊና ሃገራዊ ፍፃሜና ሁነት ተገቢው የሚዲያ ሽፋን የሚሰጥበት ሁኔታዎችን ያመቻቻል፡፡

14. Miidiyahonna dagate xaadooshshi hajora hasiisanno biddissa fushshitanno, loosu aana hosasi ha'runsitanno.
15. Qoqqowunniha mashalaqqetenna kominikeeshinete looso federaalete mootimma loosi ledo qinaawino loosu xaadooshshenna waaxo kalaqqanno, jeefissanno.

16. Gobbatenna qoqqowu deerri mashalaqqe, kominikeeshinetenna miidiyu sektere polisenna seeru qoqqowu giddo loosu aana hosansa ha'runsitanno.
17. Federaalete egensiishshu seera kaima assatenni egensiishshu loosi lifinxe buuxisate taje uytanno, ha'runsitanno.
18. Qoqqowuniha dancha su'ma kaajjishate looso loossanno.
19. Hexxose loosu aana hosiisate hasiissanno wole hajubba jeefisiissanno.

14. ለሚዲያና የህዝብ ግንኙነት የሚያገለግል መመሪያ ያወጣል፣ በስራ ላይ መዋሉን ይከታተላል፡፡
15. የክልሉን ኢንፎርሜሽን እና ኮሚዩኒኬሽን ስራ ከፌደራሉ መንግስት ስራ ጋር የሚያቀናጅ የስራ ግንኙነት እና ትብብር ይፈጥራል፤ ያስፈጽማል፡፡
16. አገራዊ እና ክልላዊ የኢንፎርሜሽን፤ የኮሚዩኒኬሽን እና የሚዲያ ሴክተር ፖሊሲዎች እና ሕጎች በክልሉ መተግበራቸውን ይከታተላል፡፡
17. የፌደራል የማስታወቂያ ህጎችን መሰረት በማድረግ የማስታወቂያ ስራ ብቃት ማረጋገጫ ይሰጣል፤ ይከታተላል፡፡
18. የክልሉን ገጽታ ግንባታ ተግባራትን ያከናውናል፡፡
19. ዓላማውን ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስፈልጉ ሌሎች ተግባራትን ያከናውናል፡፡

**R) Pilaanete Komishiine**

1. Qoqqowunnita seeda, mereerimanna harancho yanna mixo qixxeessitanno, jeefishsha ha'runsitanno, keentanno, rippoorte qixxeessatenni hajo

**ከ) ፕላን ኮሚሽን**

1. የክልሉን የረጅም፣ የመካከለኛና የአጭር ጊዜ ዕቅድ ያዘጋጃል፤ አፈፃፀማቸውን ይከታተላል፤ ይገመግማል፤ ሪፖርት በማዘጋጀት

la'annonsa bisubbara shiqishshanno.

2. Maakiro Ikkonoometenna fiizikaale hajubba mami-geeshsha qixxeessitanno, jeefisiisaanote amaale minira shiqishshe kaajjishiishshanno.
3. Qoqqowu mootimma kappitaale pirojektubba hornyi xiinxallo assitanno, keentanno, kaajjishiishshanno.
4. Qoqqowu gashshootu taqqubba dirunnita jajju beehaachi afi'ri-mala qixxeessitanno, qoqqowu amaale minira shiqishatenni kaajjishiishshanno.
5. Qoqqowunnita kappitaale pirojektubba jeefishsha ha'runsatenni keentanno, yannitte rippoorte qixxeessite hasiissanno bisubbara shiqishshanno.
6. Maakiro ikkonoomete polise jeefishshi xiinxallo ha'rissanno.
7. Qoqqowunnita latishshu xe'nenna latate dhuki xiinxallo assitanno.
8. Qoqqowinnita dagoomittenna miinju akati xiinxallo assitanno.
9. Qoqqowunnita mereerima yanna maakiro ikkonoometenna fiizikaale hajo mami-geeshsha qixxeessitanno, kaajjishiishshanno.
10. Qoqqowunita diru jiro geeshsha hedate taje qixxeessitanno፣ qoqqowu

ለሚመለከታቸው አካላት ያቀርባል፡፡

2. የማክሮ ኢኮኖሚና ፊስካል ማዕቅፍ ያዘጋጃል፤ ለመስተዳድር ምክር ቤት አቅርቦ ያስፀድቃል፡፡
3. የክልሉን መንግሥት የካፒታል ፕሮጀክቶች የአዋጭነት ጥናት ያካሂዳል፤ ይገመግማል፤ ያስፀድቃል፡፡
4. በክልሉ ለታችኛው የአስተዳደር ዕርከን ዓመታዊ የሀብት ማከፋፈያ ቀመር ያዘጋጃል፣ ለክልሉ ምክር ቤት እንዲጸድቅ ያቀርባል፡፡
5. የክልሉን የካፒታል ፕሮጀክቶችን አፈፃፀም ክትትልና ግምገማ ያደርጋል፤ ወቅታዊ ሪፖርት በማዘጋጀት አግባብነት ላላቸው አካላት ያቀርባል፡፡
6. የማክሮ ኢኮኖሚ ፖሊሲ አፈፃፀም ጥናት ያካሂዳል፡፡
7. የክልሉን የልማት ክፍተት እና የመልማት አቅም ጥናት ያደርጋል፡፡
8. የክልሉን የማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ገፅታ ጥናት ያደርጋል፡፡
9. የክልሉን የመካከለኛ ጊዜ የማክሮ ኢኮኖሚና ፊስካል ማዕቀፍ ያዘጋጃል፤ ያስፀድቃል፡፡
10. የክልሉን ዓመታዊ የሀብት ግመታ ሰነድ ያዘጋጃል፤ ለክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት በማቅረብ

jeefisiisaanote amaale minira shiqishatenni kaajjishiishshanno.

11. Qoqqowunnita miinju, dagoomittenna baattote ofolla taje gamba assitanno, maarekkitanno, tittirsha qixxeessatenni horonsi’raanote tuqissanno.
12. Qoqqowunnita dagoomittenna miinju latishshi beehaachenna baattote ofolla xawissanno atilaasenna kaarta qixxeessitanno.
13. Qoqqowu mootimma uurrinshuwa loosinsa qeechinni qixxeessitanno istatistiksete taje gamba assitanno, maarekkitanno, tittirsha assatenni horonsi’raanote iillitanno gede assitanno, hattono deerrasinna silaanchimmasi agadhino garinni qixaawanno gede irko assitanno, ha’runsatenna qorqorate looso loosanno, tajete qorqorshi gumi kaiminni hasiissanno woyyeessate qaafo adhitanno.
14. Qoqqowunnita tajete foonqe taashshate xiinxallonna buuxote looso loossanno.
15. Qoqqowunnita istatistiksete taje amanyoote yannisate mootimmate uurrinshuwara irko uytanno, looso qineessitanno, massagganno.

ያስፀድቃል፡፡

11. የክልሉን የኢኮኖሚ፣ የማህበራዊና መልክአ ምድራዊ መረጃዎችን ይሰበስባል፤ ያደራጃል፤ ትንተና በማድረግ ለተጠቃሚዎች ያሰራጫል፡፡
12. የክልሉን ማህበራዊ ኢኮኖሚያዊ ልማት ስርጭትንና የመልክዓ ምድራዊ ገፅታን የሚያሳይ አትላስና ካርታ ያዘጋጃል፡፡
13. የክልሉ መንግሥት መስሪያ ቤቶች በሥራቸው ኃላፊነት የሚያመነጩትን ስታቲስቲካዊ መረጃዎችን የማሰባሰብ፣ የማደራጀት፣ የመተንተንና ለተጠቃሚዎች ተደራሽ እንዲሆን የማድረግ እንዲሁም ስታንዳርዱንና ጥራቱን ጠብቆ እንዲዘጋጅ ድጋፍ፣ ክትትል እና ኦዲት ያደርጋል፣ በመረጃዎች ኦዲት ግኝት መሠረት ተገቢውን የማስተካከያ እርምጃ ይወስዳል፡፡
14. የክልሉን የመረጃ ክፍተት ለማሟላት የጥናትና ምርምር ሥራዎችን ያከናውናል፡፡
15. የክልሉን የስታቲስቲክስ መረጃ ሥርዓት በማዘመን ለመንግስታዊ መስሪያ ቤቶች ድጋፍ ይሰጣል፤

16. Dagaallo hajubba latishshu mixo giddo amade jeefisa lainohunni mootimmannitinna mootimmaweelo uurrinshuwa massagganno.
17. Dagaallo hajubba lainohunni dagoomunna gashshootu bisubbara huwanyo kaajjishate kaa’litanno rosunna kakayishshu looso loossanno.
18. Dagaallo latishshu hajubba laainohunni xiinxallotenna buuxote looso loossanno.
19. Qoqqowunnita dagaallo polise loosu aana hosiisate, jeefisate kaa’litanno biddissubbanna maanuwalla fushshitanno.
20. Gashshootu taqqara heedhanno dagaallote amaale minna kaajjishatenna gutamaano bisubba qineessatenni ontu dirita dagaallote pirogiraame qixxeessitanno, dagaallote amaale minira shiqishshe kaajjishiishshanno, loosu aana hosase ha’runsitanno, keennanni raga wortanno.
21. Mixotenna pirojekte qixxeessa, ha’runsanna keena lainohunni dhuka kaajjishate looso loossanno.

ሥራውን ያስተባብራል፤ ይመራል።

16. የሥነ-ህዝብ ጉዳዮችን በልማት ዕቅድ አካቶ ከመተግበር አኳያ መንግሥታዊና መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችን ያስተባብራል።
17. በሥነ-ህዝብ ጉዳዮች የማህበረሰቡንና አመራር አካላትን ግንዛቤ ለማጎልበት የሚያስችሉ የትምህርትና ቅስቀሳ ሥራዎችን ያካሂዳል።
18. የሥነ-ህዝብና ልማት ጉዳዮችን በተመለከተ የጥናትና ምርምር ተግባራትን ያከናውናል።
19. በክልሉ የስነ-ህዝብ ፖሊሲ ለመተግበር፣ ለአፈፃፀሙ የሚረዱ መመሪያዎች እና ማንዋሎች ያወጣል።
20. በየአስተዳደር እርከኑ የሚገኙትን የሥነ-ህዝብ ም/ቤቶችን በማጠናከርና ባለድርሻ አካላትን በማስተባበር የአምስት ዓመት የሥነ-ህዝብ ፕሮግራም ያዘጋጃል፣ ለሥነ-ህዝብ ም/ቤቱ በማቅረብ ያፀድቃል፣ ተግባራዊነቱን ይከታተላል፣ ይገመግማል አቅጣጫ ያስቀምጣል።
21. በዕቅድና ፕሮጀክቶች ዝግጅት ክትትልና ግምገማ ዙሪያ የአቅም ግንባታ ሥራዎችን ተግባራዊ

22. Hexxose loosu aana hosiisate hasiissanno wole hajubba jeefisiissanno.

**15. Biirote Sooreessi woy Qaru Dayrektere woy Qaru Loosaa'risaanchi woy Komishineerete Hundaanchimma, Biilloonyenna Loosi Qeecha**

1. Hundaanchimmasi uurrinsha hundaanchimmatenni galtanno mootimmate bisi sooreessira ikkitanno.
2. Qeechamino jeefisiisaanote bisi uurrinsha aliidimmatenni massaganno; yawaanchimmatenninna xa'mamaanchimmatenni loosanno.
3. Massaganno uurrinshara seerunni aamantino biilloonyenna loosu qeecha loosu aana hossanno gede ha'runsonna massagooshshe assanno.
4. Massaganno uurrinshara qeechinoonni womaashshanna jajja garunni loosu aana hosanna gede assanno.
5. Uurrinshate akati garinni gumulsha afi'rino loosaasinete seeri garinni loosaasine qaxaranno; gashshanno.
6. Uurrinsha hundaseenni galtanno uurrinshuwa afidhinoha ikkiro hundaanchimmatenni afantanno uurrinshuwara hasiissanno irkonna massagooshshe aanno.

ያደርጋል፡፡

22. ዓላማውን ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስፈልጉ ሌሎች ተግባራትን ያከናውናል፡፡

**15. የቢሮ ኃላፊ ወይም ዋና ዳይሬክተር ወይም ዋና ሥራ አስኪያጅ ወይም ኮሚሽነር ተጠሪነት፣ ሥልጣንና ተግባር**

1. ተጠሪነቱ አስፈጻሚ ተቋሙ ተጠሪ ለሆነበት የመንግስት አካል ኃላፊ ይሆናል፡፡
2. የተመደበበትን አስፈጻሚ ተቋም በበላይነት ይመራል፣ በኃላፊነትና በተጠያቂነት ይሰራል፡፡
3. ለሚመራበት ተቋም በሕግ የተሰጡ ሥልጣንና ተግባራት ሥራ ላይ እንዲውሉ ክትትልና አመራር ይሰጣል፡፡
4. ለሚመራበት አስፈጻሚ ተቋም የተመደበውን ፋይናንስ እና ንብረት በአግባቡ በሥራ ላይ እንዲውል ያደርጋል፡፡
5. እንደየተቋሙ ባህሪ ተፈጻሚ በሚሆን የሠራተኞች ሕግ መሰረት ሰራተኞች ይቀጥራል፣ ያስተዳድራል፡፡
6. ተቋሙ ተጠሪ ተቋማት ያሉት እንደሆነ ለተጠሪ ተቋማት አስፈላጊ ድጋፍና አመራር ይሰጣል፡፡

7. Sayikki bisi ledo assinanni sumiimme heedhuro uurrinsha riqiwanno; gumulsiisanno.
8. Massaganno uurrinsha galtanno bisira yannitte mixonna rippoorte shiqishanno; aamantanno taashshi'ri-tumo woy hedo loosu aana hosiisanno.
9. Uurrinshate hasiissanno baajeette la'annosi mootimmate bisira shiqishanni kaajjishiishi'ranno; fajjinirono loosoho hosiisanno; horoonsha lainohunni qorqoraanchu bisira rippoorte assanno.
10. Hasiise leelliro biilloonyisinna loosu qrrchisinni gama wolu qoqqowu woy hundasiinni noo bisira riqiwooshshunni aa dandaanno.
11. Galanno bisinni woy seerunni aamantannota lexxote assootubba wonshanno; wonshiishanno.

**16. Layinki Biirote Sooreessi woy Layinki Qaru Dayrektere woy Layinki Qaru Loosaa'risaanchi woy Layinki Komishineere woy Handaaru Sooreessi Hundaanchimma, Biilloonyenna Loosi Qeecha**

1. Hundaanchimmasi uurrinshate sooreessira ikkitanno.
2. Uurrinshate sooreessi loosu aana leellannokki yannara sooreessa riqiwe

7. ከሶስተኛ ወገን ጋር የሚደረጉ ግንኙነቶች ሲኖር ተቋሙን ይወክላል፣ ያስፈጽማል፡፡
8. የሚመራው ተቋም ተጠሪ ለሆነበት አካል ወቅታዊ ዕቅድና ሪፖርት ያቀርባል፣ የሚሰጡ ግብረ-መልሶችን ሥራ ላይ ያውላል፡፡
9. ለተቋሙ ሥራ የሚስፈልገውን በጀት ለሚመለከተው የመንግስት አካል እያቀረበ ያጸድቃል፣ሲፈቀድም ሥራ ላይ ያውላል፣ ስለአጠቃቀሙ ለተቆጣጣሪ አካል ሪፖርት ያቀርባል፡፡
10. አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ከሥልጣኑና ተግባሩ በከፊል ለሌላ የክልል ወይም የበታች አካል በውክልና ሊሰጥ ይችላል፡፡
11. ተጠሪ ከሆነበት አካል እና በሕግ የሚሰጡ ተጨማሪ ተግባራትን ይፈጽማል፣ ያስፈጽማል፡፡

**16. ምክትል የቢሮ ኃላፊ ወይም ምክትል ዋና ዳይሬክተር ወይም ምክትል ኮሚሽነር ወይም ምክትል ሥራ አስኪያጅ ወይም የዘርፍ ኃላፊ ተጠሪነት፣ ሥልጣንና ተግባር**

1. ተጠሪነቱ ለአስፈጻሚ ተቋሙ ኃላፊ ይሆናል፡፡
2. የተቋሙ ኃላፊ ሥራ ላይ በማይገኝበት ጊዜ ኃላፊውን ተክቶ በኃላፊነትና በተጠያቂነት ይሰራል፡፡

yawaanchimmatenninna xa’mamaanchimmatenni loosanno.

3. Konni quwira cinaanchu quwi 1ho worroonnihu noo gedeenni mittu aleenni layinkihu noo uurrinshara borrote riqiwonni aamantino woy borrote riqiwooshshi aamaminokki yannara layinki loosu massagaanchimmanni balaxe qeechamini sooreessi riqiwe loosanno.
4. Uurrinshunni qeechamino looso gumulanno; gumulsiisanno.
5. Hundasiinni afantanno loosaasine bobbaasanno; irkisanno; qorqoranno.
6. Sooreessunni aamamannoha lexxote looso loosanno; loosiisanno.

## Gafa Shoole

## <u>Addi Addi Woro</u>

**17. Jeefisiisaano Bisubbanna Hundanni Galtanno Jeefisiisaano Bisubba Gashshootu Taqqara Heedhanonsa Tantano Lainohunni**

Konni lallawira quwa 9 woy 10 garinni uurrinsoonniri jeefisiisaano bisubba qoqqowu giddo afantanno gashshootu taqqara hasiisi garinni tantano heedhansara danditanno. Tittirshu qoqqowu jeefisiisaanote amaale mini fushshanno wodhonni muramanno.

3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ከአንድ በላይ ምክትል ባለበት ተቋም በጽሁፍ ውክልና የተሰጠው ወይም የጽሁፍ ውክልና ባልተሰጠ ጊዜ በምትክል የሥራ መሪነት ቀድሞ የተመደበ ኃላፊን ተክቶ ይሰራል፡፡
4. በቋሚነት እንዲመራ የተመደበበትን ሥራ ይፈጽማል፣ ያስፈጽማል፡፡
5. በሥሩ የሚገኙ ሠራተኞችን ያሰማራል፣ ይደግፋል፣ ይቆጣጠራል፡፡
6. በኃላፊ የሚሰጡ ተጨማሪ ተግባራትን ይፈጽማል፣ ያስፈጽማል፡፡

## ክፍል አራት

## <u>ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች</u>

**17. አስፈጻሚ እና ተጠሪ አስፈጻሚ አካላት በየአስተዳደር እርከን ስለሚኖራቸው አደረጃጀት**

በዚህ አዋጅ አንቀጽ 9 ወይም 10 መሠረት የተቋቋሙ አስፈጻሚ አካላት በክልሉ ውስጥ በሚገኙ የአስተዳደር እርከኖች እንደ አስፈላጊነቱ አደረጃጀት ሊኖራቸው ይችላል፡፡ ዝርዝሩ መስተዳደር ምክር ቤት በሚያወጣው ደንብ ይወሰናል፡፡

**18. Shiikkaancho Woro**

Konni lallawi garinni uurrinsoonniri jeefisiisaano bisubbanna hundaani galtanno jeefisiisaano bisubba gashshootu taqinni tantanonsa kaajjite looso hanaffa geeshsha bashsho jeefisiisaano bisubba tantano loosose sufanno.

**19. Wodhonna Biddissa Fushsha Lainohunni**

1. Konne lallawa loosoho hosiisate hasiissanno wodho qoqqowu jeefisiisaanote amaale mini fushshara dandaanno.
2. Konne lallawanna lallawa ha’runsite fultino wodho gumulsiisate biddissuwa konni lallawira quwa 9 garinni uurrinsoonniri jeefisiisaano bisubba fushshitara dandiitanno.

**20. Gumulaachimma Heedhannosikki Seeranna Assoote**

Konne lallawa ledo kiphamanno aye seeri woy assooti konni lallawinni kamalantino hajora gumulaanchimma dinose.

**18. የመሸጋገሪያ ድንጋጌ**

በዚህ አዋጅ መሠረት የተቋቋሙ አስፈጻሚ እና ተጠሪ አስፈጻሚ አካላት በየአስተዳደር እርከኑ አደረጃጀታቸው ተጠናክረው ሥራ እስከሚጀምሩ ነባሩ የአስፈጻሚ አካላት አደረጃጀት ሥራውን ይቀጥላል፡፡

**19. ደንብና መመሪያ ስለማውጣት**

1. ይህንን አዋጅ ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስፈልግ ደንብ መስተዳደር ምክር ቤት ሊያወጣ ይችላል፡፡
2. ይህንን አዋጅ እና አዋጁን ተከትሎ የወጣ ደንብን ለማስፈጸም የሚያስፈልጉ መመሪያዎችን በዚህ አዋጅ አንቀጽ 9 መሠረት የተቋቋሙ አስፈጻሚ አካላት ሊያወጡ ይችላሉ፡፡

**20. ተፈጻሚነት ስለማይኖረው ሕግና አሰራር**

ይህንን አዋጅ የሚቃረን ማንኛውም የሕግ ሠነድ ወይም አሰራር በዚህ አዋጅ ለተሸፈኑ ጉዳዮች ተፈጻሚነት የለውም፡፡

**21. Lallawu Kaajjanno Yanna Laiohunni**

Kunni lallawi Ella **29** barrinni 2012 M.D hanafe kaajjinoha ikkanno.

**Hawaasa, Ella 29, 2012 M.D**

**Desta Ledamo**

**Sidaamu Dagoomu Qoqqowi Mootimma Pirezidaanticha**

**21. አዋጁ ስለሚጸናበት ጊዜ**

ይህ አዋጅ ከሰኔ ፳፱ ቀን ፳፻፲፪ ዓ.ም ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡

ሀዋሳ፣ ሰኔ ፳፱ ቀን ፳፻፲፪ ዓ.ም

ደስታ ሌዳሞ

የሲዳማ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ርዕሰ መስተዳደር